**በአንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትሕ ፓርቲ (አንድነት)**

**ም/ሊቀመንበርና የውጭ ጉዳይ ኃላፊ 1ኛ ዓመት የምሥራታ በዓል ላይ**

**በዶ/ር ያዕቆብ ኃ/ማሪያም የተደረገ የመዝጊያ ንግግር**

# የአንድነት ፓርቲ ሊቀመንበር ወ/ት የብርቱካን እስርና የወቅቱ የአገራችን ሁኔታ

ክቡራትና ክቡራን!

አንድ ጥያቄ ልጠይቃችሁ እፈልጋለሁ:: መልሱን አታውቁትም ሳይሆን የሚወዱንም የሚጠሉንም የፖለቲካ ባላንጣቻችን ሆኑ አጋሮቻችን በጠቅላላው ዓለም እንዲያወቀው ነው አዲስ አበባም እንዲሰማው ጮክ ብላችሁ መልሱልኝ:: አሁንም የአንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትሕ ፓርቲ ሊቀመንበር ማን ነች:: (ታዳሚው ሦስት ጊዜ ብርቱካን ነች ብሎ መለሰ)

ክቡራትና ክበራን!

በ1412 ዓም በፈረንሳይ አገር አንዲት ልጅ ከድሀ ገበሬ ቤተሰብ ተወለደች:: ልጅቷ ገና ከሕፃነትዋ ጀምሮ የአገር ፍቅር የሰረፀባት፤ ለድሀ አዛኝ፤ በጣም አስተዋይና ቁም ነገረኛ ፍርሀት የሚባል ነገር ፍፁም የማታውቅ ልጅ ነበረች:: ገና በ12 ዓመትዋ በከፊል በእንግሊዝ ተይዞ የነበረው አገርዋ ነፃ እንድታወጣ የሚያሳስቡአት ድምፆች ትሰማ እንደነበር ትናገር ነበር:: ይህንኑ ከመንበሩ ተባሮ ለነበረው ንጉሱ ነግራ አገርዋን ነፃ እንድታወጣ ንጉሱም እንዲፈቅድላት በእጅጉ ተማጠነችው:: ንጉሱም ፈቅዶላት በ19 ዓመትዋ የፈረንሳይ ጦር እየመራች እንግሊዞች ከፈረንሳይ ግዛት እንዲወጡ በመጀመሪያ ስታስጠነቅቅ እንግሊዞችም በዚች ጨጬ ድፍረት ተበሳጩ:: እንግሊዞች ፈረንሳይን አንለቅም፤ በማለታቸው በዚች ልጅ የሚመራው የፈረንሳይ ጦር ገጥመው ሲሸነፉ ልጅቷ ደረቷ ላይ በቀስት ተወግታ ወደቀች:: ሆኖም ጦሩን መርታ አገርዋን ነፃ አወጣች::

ምቀኞችና ግፈኞች ከ14 ዓመት እድሜዋ ጀምሮ የሚያናግሩአት ድምፆች ማዳመጥ የመናፍቃን ድርጊት ነው በሚል ልጅቷ እንድተፀፀትና ቃልዋን እንድትለውጥ ብትጠየቅ አሻፈረኝ አለች:: በመጨረሻም ቃልዋን እንድታጥፍ ሁለት ቀናት ቢሰጣትም አልበገርም አለች:: ስለዚህ በመናፍቅነት ተከስሳ ጥፋተኛ ነች ተብላ በጊዜው መናፍቃን ይቀጡበት በነበረው መንገድ በእሳት ተቃጥላ ሞች:: ዛሬ ጆን አብ አርክ በአገሯ አጠራር Jean D'arc አገርዋን ነፃ ያወጣች ቆራጥ ጀግና ተብላ ሀውልቷ በፈረንሳይ ከተሞች ተተክለው ስሟ ሕያው ሆኖ የሚኖር በፈረንሳይ ታሪክ ጥቂት ተወዳዳሪች ያላት ጀግና ተብላ እየተዘከረች ትኖራለች:: በካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ሥርዓትም ቅድስትም ተብላለች::

ዛሬ የእኛዋ የፓርቲያችን ሊቀመንበር ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ በቆራጥነት በአገር ፍቅር ጽናት ከፈረንሳይቷ ጆን ኦፍ አርክ የምትለየው እንደ ፈረንሳይቷ ጦር ሰብቃ፤ ሻምላ ታጥቃ የጦር ልብስ አጥልቃ ሳይሆን የሰላም ዘንባባ ይዞ በአገራችን ሠላም ይሰፍን፤ ፍቅር ይንገስ ጥላቻ ይወገድ፤ ዴሞክራሲ ያብብ፤ የሕግ የበላይነት ይከበር በማለት ከጆን ኦፍ አርክ ያላነሰ ዓላማ አንግባ እንደ ጆን ኦፍ አርክም ቃሌን አላጥፍም በማለትዋ ጆን ኦፍ አርክ ለሞት ስትዳረግ የእኛዋ ወህኒ አወረዱአት::

የሊቀመንበራችን ዳግም መታሰር ፍፁም ሕገ-ወጥ ድርጊት መሆኑ በተደጋጋሚ ገልፀናል:: ለማስታወስ ያህል በአጭሩ ልጠቅሰው ይፈቀድልኝ:: በሕጉ ከሄድን ወይዘሪት ብርቱካን አንድ ቀን ወህኒ ቤት የሚያሳድራት የሕግ ጥሰት የለም::

ወ/ት ብርቱካን ልትታሰር የምትችለው የቅንጅት አመራሮችና ወ/ት ብርቱካንም ጭምር የገባችው ግዴታ በመጣስ ሕገ መንግሥቱና ሕገ መንግሥታዊ ሥርዓቱን በኃይል ለመለወጥ ሞክራ ቢሆን፣ በሕገ-መንግሥቱ የተደራጁ የመንግሥት አካላት ሥልጣንና ተግባር ተቀብላና አክብራ ባትገኝ፣ ከመጀመሪያው እስር የተፈታችበት ቅድመ ሁኔታ ሰለጣሰች የአሁኑ እስርዋ ሕጋዊ ነው ማለት በተቻለ ነበር:: ሊቀ መንበራችን የታሰረችው ከእነዚህ ከገባችባቸው ግዴታች አንዱንም ጥሳለች በሚል ሳይሆን በስዊድን ለአንድነት ፓርቲ ደጋፊች ባደረገችው ንግግር ነው:: የተባለው የስዊድን ንግግሯ ምንም ያህል ቢለጠጥ ሕገ-መንግሥቱን በኃይል መናድ ነው ሊባል አይቻልም:: ወይንም ከዚህ በላይ ከተዘረዘሩት ቅድመ ሁኔታች አንዱም ላይ አይወድቅም:: ሊቀመንበራችን በስዊድን ያደረገችው ንግግር ምንም ትበል ምንም በሕገ- መንግሥቱ በአንቀጽ 29 ውስጥ የሚወድቅ ነው:: ይኸው አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 ሲቀረጽ የወ/ት ብርቱካንን የአሁኑ ሁኔታ ታስቦ የተፃፈ ይመስላል:: አንቀፁን እጠቅሳለሁ:: «ማንኛውም ሰው ያለ ማንም ጣልቃ ገብነት ሃሳቡን የመግለጽ ነፃነት አለው:: ይህ ነፃነት በሀገር ውስጥም ሆነ ከሐገር ውጭ ወሰን ሳይደረግበት በቃልም ሆነ በጽሁፍ ሃሳብን የመቀበልና የማሰራጨት ነፃነቶችን ያካትታል» ሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ 17 ደግሞ በሕግ ከተደነገገው ሥርዓት ውጭ ማንኛውም ሰው ነፃነቱን እንደማያጣ ያረጋግጣል:: በመቀጠልም ማንኛውም ሰው በሕግ ከተደነገገው ሥርዓት ውጪ ሊያዝ ክስ ሳይቀርብበት ወይንም ሳይፈረድበት ሊታሰር እንደማይችል ይደነግጋል:: ሊቀመንበራችን ምንም የጣሰችው ሕግ ሳይኖር ታሰረች:: አዲስ ወንጀል ሠርታለች ከተባለም ክስ ሳይቀርብበትና ሳይፈረድባት ለእስራት ተደርጋለች:: የይቅርታው መስረዝም ፍፁም ሕግን ያልተከተለ እንደነበረ በተለያዩ ወቅቶች ስለ አስረዳሁ አሁን አልመለስበትም::

በአገራችን የሕግ የበላይነት ደብዛው ጠፍቶአል ስንል በመንግሥት ላይ የታሰነዘረ ተራ የተቃዋሚ ፓርቲ ስም ማጥፋት ወይንም ሃሜት አይደለም:: ይህንን የምንለው ከተጨባጭ እውነታች ተነስተን ነው:: ይህንንም ለመረዳት የሕግ ጠበብት መሆን አያሻም::

የወ/ት ብርቱካን ይቅርታን ሰርዞ ዳግም መታሠር አንዱ የሕግ የበላይነት ጥሰት ሆኖ ሌላው ደግሞ ከሁለት ወራት በፊት የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት የሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 21 መሠረት በማድረግ የወ/ት ብርቱካን ከቅርብ ዘመዶችዋ፣ ከጓደኞችዋ፣ ከኃይማኖትና ከግሕ አማካሪጂ ጋር በመገናኘት የመጎብኘት መብት እንዳላት ገልፆ፣ ጉብኝቱ እንዲተገበር ፍ/ቤቱ ለሚመለከተው የመንግሥት አካላት ሁለት ጊዜ ጥብቅ ትእዛዝ ቢያስተላልፍም መንግሥት ትእዛዙን ከቁብ ባለመቁጠር እስከ ዛሬም የፍርድ ቤቱ ትእዛዝ አልተፈፀመም:: አንድ ሰው በደል ደርሶብኛል ብሎ ለፍ/ቤት አመልክቶ ፍ/ቤት ትእዛዝ ሲሰጠ ትእዛዙ በመንግሥት ካልተፈፀመ ወዴት ይኬዳል:: ምላጭ ቢያብጥ በምን ይበጣል፣ እንደሚባለው እባጩን ለማፍረጥ የተፈጠረው ምላጭ እራሱ ካበጠ የሚከተለው የእባጩ በራሱ መፈንዳት ሲሆን ፍትሕም የተነፈገ ሰው ሌላ አማራጭ ከመሻት ምን ምርጫ አለው? እንደዚህ ዓይነቱ ተበዳይ ሕጉ፣ በእጁ በማግባት በደሉን ለማስወገድ ሕገ-ወጥ በሆነ መንገድም ቢሆንም መጣሩ አይቀርም::

ለብርቱካን እስር አዲስ ነገር አይደለም:: በእሳት ተፈትና ነጥራ የወጣች የዴሞክራሲ አርበኛ እንደመሆንዋ መጠን እስር በግሯት ለትግል ያላት ቆራጥነት ይሚሸሻል፣ ወኔዋ ይከዳታል ብለው የሚያምኑ አሳሪጂ ብርቱካን መንፈሰ ጠንካራና በጽናት የምትቆም መሆንዋ ማን በነራቸው? በአንድ አገር ዴሞክራሲ እንዲሰፍን፣ ሰብአዊ መብቶች እንዲከበሩ፣ የሕግ የበላይነት እንዲነግስ የታጋዮች መታሰር ቀርቶ አንዱ ታጋይ በሌላው

እሬሳ ተረማምዶ ትግሉን መቀጠል አስፈላጊ የሚሆንበት ጊዜ መኖሩ ብርቱካን ጠንቅቃ ታውቃለች፡፡

የብርቱካን መታሰር የአንድ ግለሰብ ወይንም የአንድ ፓርቲ መሪ መታሰርም ብቻ አይደለም፡፡ ብርቱካንን ማሰር ሴቶች እህቶቻችን ወይንም ልጆቻችን በአገራቸው ዴሞክራሲ እንዲሰፍንና የሕግ የበላይነት እንዲከበር የሚያደርጉት ተነሳሽነት ማሰር ነው፡፡ በአገራችን አንድን ፓርቲ በመምራት በሴትነቷ ፋና ወጊ የሆነችዋን ሊቀመንበራችንን ማሰር የመላው የኢትዮጵያ ሴቶች ራዕይ ማሰር ነው፡፡ ብርቱካንን ማሰር ሠላማዊ ትግሉ አበቃለት፣ በፈለጋችሁት መንገድ ሂዱ መንገዱንም ጨርቅ ያድርግላችሁ እንደማለት የሚቆጠር ነው፡፡

ፓርቲያችን በተለያዩ ጊዜአት ገዢው ፓርቲ የሚያራምደው የፍጥጫ፣ የጭጭ በሉ፣ አፋችሁን ሸብባችሁ ሕሊናችሁን ዘግታችችሁ ተገዙ የሚለው አካሄድ የሰውን ተፈጥሮ የሚቃረን መሆኑና ለገዢው ፓርቲም ሆነ ለአገራችን እንደ ማይበጅ በተደጋጋሚ በተለያዩ ወቅቶች ገልፀናል፡፡ ፓርቲአችን በተለያዩ ጊዜአት ከገዢው ፓርቲ ጋር ያለንን ግንኙነት ሠላማዊ የሰከነ በእኩልነትና በመከባበር ላይ የተመሠረተ፣ እንዲሆን የፖለቲካ ልዩነቶቻችን እንደተጠበቁ ሆነው በመተባበር በመተጋገዝ ሕዝባችንን ለዴሞክራሲ እናብቃ አሳፊሪ የሆነው ድህነታችንን በጋራ እንዋጋው ብለን የሠላም እጃችንን በዘረጋን ቁጥር የሚጠብቀን ያንን የዘረጋውን እጅ መቁረጥ ነው ሆነ፡፡ ጥሪአችን አሁንም አያባራም አሁንም ሊቀመንበራችንን በአስቸኳይ ከእስር መፍታት ለጥሪአትን አንታዊ ምላሽ መስጠት አድርገን እንቆጥረዋል፡፡

ክቡራንና ክቡራት!

አገራችን እጅግ አደገኛ በሆነ መንገድ ላይ እየተጓዘች ትገኛለች፡፡ በተለይ በተማሪው መሀከል ጥላቻ፣ መቃቃር፣ የጎሪጥ መተያየት እየተስፋፋ እየሄደ ነው፡፡ ጥላቻው እጅግ ተካሮ ወደ ዘር ጭፍጨፋ የተሸጋገሩ አገሮች ወደዚያ አቅጣጫ እያመሩ መሆናቸው አንዳንድ ሰች ቢያስጠነቅቁም ይህንን ማስጠንቀቂያ ገዢች ባለማዳመጣቸው አሰቃቂ ክስተቶች ተፈጥረዋል፡፡ ጥላቻው ያስከተለው እልቂት በዓይኑ እንዳየ ሰው ምንም ይምጣ ምንም ይህንን ማስጠንቀቂያ ሳይዘገይ የማሰማት ልዩ ኃላፊነት እንዳለብኝ ይሰማኛል፡፡ ይህ ጥላቻ እያቆጠቁጠ መሄዱን የሚክዱ ሰች ቢኖሩ አውሎ ነፋስ እየመጣ አላየሁም ፣የለም ብላ አንገቷን አሸዋ ውስጥ በቀረቀረች ሰጎን ይመሰላሉ፡፡ በሕዝባችን መሀከል መግባባት፣ ሠላም፣ ፍቅር፣ እንዲሰፈን የተጀመረው ጥላቻ እንዲከስም የሁላችን ጥረት በተለይም የመንግሥት ጥረት ይጠይቃል፡፡

እኛ ኢትዮጵያውያን አለመታደል ሆኖ አደገኛ በሆነ አካባቢ ሰፍረናል፡፡ በአንድ ጆምበር ጠፍተን ብናድር በደስታ በሚፈነድቁ ኃይሎች ተከብበናል፡፡ ይህ ደግሞ ከኃይማኖት ጋር ምንም ግንኙነት የለውም፡፡ አገራችን እኩል የክርስቲያንም የሙስሊምም የይሁዲም አገር ነች፡፡ በተጨማሪም በኑክሌር ቦምብ በቅርብ ቀን የምታጠቅ አንዲት አገር ጓሮአችን አሰብ ላይ ጦሯን አስፍራለች፡፡

አጥፊቻችን ልንቋቋማቸው የምንችለውና በአንድ ፓርቲ በአንድነትም ይሁን በኢህአዴግ ጥረት ብቻ ሊሆን አይችልም፡፡ በእያንዳንዳችን ጥረትና ትብብር ብቻ ነው፡፡ በተጨማሪም የምሥራቅ የአፍሪቃ የውሀ ገንዳ ሆነን ችጋርን አሁንም ማሸነፍ አልቻልንም፡፡ ከስንዴ ልመናም አልወጣንም፡፡ የጎደለን ምንድን ነው ቢባል? የጎደለን ብሔራዊ መግባባት ነው፡፡ የጎደለን እራሳችንን እረስተን አገራችንና ሕዝባችን በእኛነት መተካት ነው፡፡

እግንዲህ ለአንዴና ለሁሌም የዛሬቹ ኢትዮጵያውያን እንደጧፍ ነድደን ለነገው ትውልድ ብርሃን ሰጥተን ኢትዮጵያ የዓለም የመጨረሻዋ ድሀ ነች የሚባለው ማክተም አለበት። በኢትዮጵያ ዴሞክራሲ ሰፍኖ የሕግ የበላይነት ተከብሮ አያውቅም የሚባለው በእኛ ጊዜ ይብቃ። ኢህአዴግ ለዚህ ጥሪአችን ቅንጣት ያህል ዋጋ የሚሰጥ ከሆነ ሊቀመንበራችንን ከእስር በመፍታት ያስታውቀን። የሚመጣው ዓመት በሊቀመንበራችን ሰብሳቢነት አንዳችንም ሳንጓደል በዴሞክራሲያዊ አገራችን ለመገናኘት ያብቃን።

እግዚአብሔር ኢትዮጵያን ይታደጋት!